PANORAM # 5

## የትዝብት አድማስ

ታህሳሥ 20 2007

## ኢትዮጵያና አይታክቴ ጠላቶቿ

ከአራት ወራት በፊት በተከበረው የኢትዮጵያ የሁለት ሺ ዘመን መለወጫ በዓል ላይ አንድ ኢትዮጵያዊ አዛውንት ምሁር በሰጡት አስተያየት የሚከተለውን ትዝብት መሰንዘራቸው ትዝ ይለናል፡፡ ከሞላ ገደል የተናገሩት ይህንን ይመስላል ነበር፡፡

" የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ቁንጅና የጠላቶቿን ዓይን ስለሚስበው፥ ዘለዓለም ከእነርሱ ጥቃትና ትኩረት ልትላቀቅ አልቻለችም፡፡" ብለዋል፡፡

ምናልባት የእኝህን አዛውንት ምሁር ንግግር በትክክል መጥቀስ ካልቻልን፥ በቅድሚያ ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብትና ውበት፥ የበለፀገ ታሪክና ባህል ባለቤትነት፥ እንዲሁም በጅዖ-ፖሊትክስ ማለትም ካለችበት ቦታ ጠቀሜታዋ ምክንያት የባዕዳንን ቀልብ መስህብ ሆኗ ቆይታለች፡፡ ይህ ክስተት ደግሞ ሀገሪቱን፥ በተለያዩ ዘመናትና የታሪክ አጋጣሚዎች የቅኝ ገዥዎችና የባዕዳን ወረራ ሰለባ ሆነ ቆይታለች፡፡ ቆንጆ ሚስት ያለው አባወራ፥ የባለቤቱን ፍፁም ታማኝነት በማያጠራጥር መልኩ እስኪያረጋግጥ ድረስ፥ በዕውነትም ይሁን ወይም በአንደምታ ከስጋት ነፃ ሊወጣ እንደማይችል ሁሉ፥ በውበቷና በፀጋዋ የተደነቀች ሀገር ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብም፥ በቂ የመከላከያ ኃይልና ጉልበት መኖሩን እስካላረጋገጠ ድረስ ሁል ጊዜ በሀገሩ ቁንጅና ምክንያት ከሚያቋምጡ ጠላቶች በኩል ስለሚቃጣው አደጋ ዕረፍት እንደማያገኝ ጥርጥር ሊኖር አይችልም፡፡

እረ ለመሆኑ፥ የኢትዮጵያ ቁንጅና ለባዕዳን ፍላጎትና ቀልብ እንዴት መስህብ ሊሆን ቻለ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ፥ ይህንን መልስ በማያወላውል መንገድ ሊሰጥ የሚችለው ያው ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው፡፡ ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው፥ እንደሚባለው፥ ሌላ ሰው ስለኢትዮጵያ መናገር የሚችል አይደለም፡፡ የሀገሪቱን የተፈጥሮ ውበትና ሀብት ፥ አየሩን፥ አፈሩን፥ ወንዞቹን፥ ከመሬት በላይ ያለውን የተፈጥሮ ሀብትና በከርሰ ምድር ያለውን ማዕደን ለማግኘት እስከዛሬ ድረስ ያልተደረገ ጥረት አልነበረም፡፡ ይህን ገና ያልተነካና ያልተበዘበዘ ሀብት ፈላጊው፥ ቁጥሩ ኅልቆ መሳፍርት የሆነ ነው፡፡ ፈላጊው የበዛ ሁሉ ደግሞ የፈለገውን ለማግኘት ስለሚረባረብ ከፍተኛ መራኮት እንደሚያደርግና በዚያው መጠን የሚያሳየው ጠላትነት የመረረ ይሆናል፡፡ የሀገራችንን ውበት፥ ሀብትና ንብረት፥ የጆግራፊያዊ አቀማመጥ ጠቀሜታ

ለመቆጣጠር በዘመናት ይህ ነው የማይባል ፍጅትና ዕልቂት እንደተደረገ የሚካድ አይደለም፡፡ “በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል” ነው መሰል፥ ከቅርብ ዘመናት ወዲህ የተለዋወጡት የኢትዮጵያ መሪዎች የሀገራቸውን ውበት፥ ሀብት፥ ንብረትና ህልውና በቅጡ ባለመያዛቸው ወይም ለመያዝ ባለመቻላቸው፥ ኢትዮጵያ የማንም መጫወቻና ሰለባ ሆና ቀረች፡፡ ጠላቶቿ ደግሞ ይህንን ሁኔታ በመጠቀም እስካዛሬ ድረስ ሀገራችንን በዓይነ ቁራኛ ከማየት አልፈው ተርፈው፥ ተስፋ ሳይቆርጡ እስከመጨረሻው የሚለቋት አይመስልም፡፡ አትዮጵያን የሚታደጋት ኢትዮጵያዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እስከተመሠረተ ድረስ፥ ብሎም የኢትዮጵያ ሁሉ-አቀፍ ጥንካሬ፥ አስተማማኝ ደረጃ እስከሚደርስ ጠላቶቿ ለማዳከምና ከቻሉም ለመበታተን የሚተኙ አይደሉም፡፡

የኢትዮጵያ ውበትና ቁንጅና በዘመን ብዛት የማይወይብ፥ ታሪኳ የማይከለስ፥ ባህሏና ዕምነቷ የማይበረዝ፥ ስፋቷ የማይለወጥ፥ አየሯ የማይበከል፥ ሕዝቧ የማይለወጥ፥ ዳር ድንበሯ የማይደፈር፥ የመልከአ-ምድሯ ይዞታዋ የተለየ መልክና ሁኔታ እንደማይዝ አድርጎ መቀበል፥ “ያልጠረጠረ ተመነጠረ” መሆን ነው፡፡ የወያኔ ብሄረተኛ ቡድን በማን ድጋፍና ትብብር ለሥልጣን እንደወጣ የአደባባይ ምሥጢር ስለሆነ፥ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሀገራችን ይህንን ሂደት እንድትከተል ማነኛውንም ጥረት ሊያደርጉ አይችሉም ብሎ ገላ-ሰዶ መቀመጥም፥ የኋላ ኋላ “ወይኔ እጄን በእጄ በላሁት” እያሉ የዘለዓለም ፀፀት ሰለባ መሆን ነው፡፡ በዕርግጥ ሀገራችን አሁን በያዘችው የጥፋት ጎዳና እንድትቀጥል ከተደረገና የውስጥና የወጭ ጠላቶቿን የጥቃትና የመሰሪ ዕቅድ ማክሸፍ ካልተቻለ፥ ሃገር ወዳድ የሚባል ቅፅል ለማነኛው ዜጋ ሊሰጥ የሚገባው አይመስለንም፡፡ ይህንን ለማለት የደፈርነው፥ የሀገር ወዳድነት የመጀመሪያው ትርጉም ለሀገር ቀናዒ መሆንና ካስፈለገም መስዋዕት መክፈል ነው ብለን በማመናችን ነው፡፡

ከሀገራችን ውበቶችና ቁንጅናዎች ውስጥ በቅድሚያ ጎልተው ከሚታዩት መካከል የመጀመሪያዎቹ፥ የኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞች ናቸው፡፡ ወንዞቻችን፥ የኢትዮጵያ የመኖር ዘመን መቆጠር ከተጀመረ አንስቶ፥ ለሕዝቦቿ አንዳችም ጥቅም ሳያበረክቱ ለባዕዳን ሲሳይ ሆነው ቆይተዋል፡፡ ምናልባት መስጠት ከሚገባቸው ጠቀሜታ እጅግ ሲበዛ በጣም አነስተኛ መጠን ግልጋሎት ሰጥተዋል የሚባሉት ቆቃና አዋሽ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሌሎች ግን እስካሁን በጥቅም ላይ አልዋሉም፡፡ አልጠቀሙም ተብለው ግን ሊወቀሱ ሊነቀሱ አይችሉም፡፡ ለጥቅም ያዋለቻቸው ሰው የለምና! ተከዜ፥ ገናሌ፥ ጊምቢ፥ አንገረብ፥ ዋቢ-ሸበሌ፥ ዐባይ፥ መረብ፥ ወይና፥ በለገዝ፥ አንጎባ፥ ጓንግ ወዘተረፈ ሥራ ፈትተው ይኖራሉ፡፡ ለሕዝብ ጥቅም ባለማዋለቸው ሕዝቡን በትዝብት ይመለከቱት እንደሁ እንጅ፥ በከንቱ በመፍሰሳቸው ምክንያት የኀሊና ወቀሳ ይይዛቸዋል ለማለት አንደፍርም፡፡ ከሁሉም በላይ እንደ እግር እሳት ሊያንገበግቡ የሚችሉት ግን የአባይና የዋቢ ሸበሌ ነገርና በኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት የሚያካሂዱት ያልተቋረጠ ዘረፋና ከጠላት ጋር የሚያደርጉት መተባበር ነው፡፡ በተለይ የዐባይ ወንዝ ጉዳይ ሲነሳ ኢትዮጵያዊው ሁሉ

ሊቆጭና ሊበሳጭ የሚችልበት አስገዳጅ ምክንያቶች አሉ። ምክንያቱም የዐባይ ተጠቃሚ ሀገራት፥ “ ከሞኝ በራፍ ብልህ ሞፈር ይቆርጣል” እያሉ ስለሚያፌዙብን ነው። ዐባይ፥ ለሱዳንና ለምስር ወይም ግብፅ ሕዝቦች የሚሰጣቸው ሁለንተናዊ ጥቅም በሞትና በሽረት ደረጃ የሚመዘን ነው። የኢትዮጵያን ውሃ ብቻ ሳይሆን፥ ለም አፈሯንም ጭምር በገፍ ስለሚለግሳቸው፥ እነኝህ ሁለት ሀገሮች ለዐባይ የሚሰጡት ፍቅርና ምስጋና እስከ ደማቸው ጠብታ ድረስ ዋጋ የሚከፍሉበት ነው። ስለ ዐባይ፥ በዘመናት ብዙ ስንክሳር የተፃፈና የተደረሰ በመሆኑ፥ እኛ ዛሬ በዚህ ላይ የተለየ ነገር ለመጨመር አንሞክርም።

ግን አንድ የንፅፅር አስተያየት ሰጥተን ለማለፍ እንፈልጋለን። የአባይ ወንዝ ከግብፅ ግዛት ከገባ ጀምሮ ሜዴትራንያን ባህርን እስከሚቀላቀል ድረስ፥ ግብፆችን በመስኖ፥ በርሻ፥ በከብት ርቢ፣ በኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፥ እና በመሳሰሉት የሀገሪቱ የኢኮኖሚክ አውታሮች ተዘርዝሮ የማያልቅ አገልግሎት ይሰጣል። በአባይ ወንዝ ምክንያት ግብፆች በዓመት አራት ጊዜ የርሻ ሰብል ያመርታሉ። በመሆኑም ለምልዓተ ሕዝቡ የሚሆን የምግብ አቅርቦት በገፍና በርካሻ ዋጋ ይታደላል። በአባይ የውሃ መስኖ የሚመረተው የግብፅ ጥጥ፥ የሀገር ውስጥ ፍጆታውን አርክቶ በውጭ ገበያም ከፍተኛ ጥራት ያለውን የጥጥ ዓይነት ያቀርባል። ከሰማኒያ ሚሊዮን በላይ የሆነው የግብፅ ሕዝብ በቂ ተመጋቢ ከመሆኑም በላይ፥ ለመካከለኛው ምሥራቅ የማይናቅ የርሻ ውጤት ይልካል። በዐባይ ውሃ የተመላው የአስዋን ግድብ፥ በታላቅነቱ በዓለም ካሉት ግድቦች አንዱ ነው። ከግድቡ በሚገኘው የኤሊክትሪክ ኃይል ሁሉም የግብፅ ቤተሰብ ተጠቃሚ ነው። ከገጠር እስከ ከተማ ያለው የግብፅ ቤተሰብ የኤሌክትሪክ መብራት ያገኛል ብንል የተጋነነ ነው ማለት አይቻልም። ለካስ ግብፅ የዐባይ ስጦታ ወይም ገፀ በረከት ነች ተብሎ የተፃፈው ዕውነት ኖሯል እባካችሁ?

ዐባይ የሚፈልቅባትና የዐባይ ጌታ የሆነችው ኢትዮጵያ በማንኛውም የኢኮኖሚና የልማት ዕድገት ስትለካ፥ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ማለትም በኢትዮጵያና ግብፅ መካከል የሰማይና የምድር ያህል ርቀት መኖሩን መካድ አንችልም። ግብፅና ሱዳን የኢትዮጵያን መድከም፥ መክሰምና መበታተን ከሚፈልጉት ሀገሮች የመጀመሪያውን ደረጃ ማያዛቸው አያስደንቀንም። ወያኔን ለሥልጣን ካበቁት ሀገሮች፥ ግብፅና ሱዳን ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱት ናቸው። ይህን ሁሉ የምናወሳው፥ ይህ ሀቅ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰወረ በመሆኑ ሳይሆን፥ በርዕሱ እንደተጠቀሰው፥ ኢትዮጵያ በውበቷ፥ በሀብትና በማንነት የቱን ያህል የጠላቶቻችን ሰለባ እንደሆነች ለመጠቆም ብቻ ነው። ክረምት–ተበጋ ሳያቋርጡ የሚፈስሱ ታላላቅ ወንዞች እያላት ሀገር፥ በአራቱ የዓመት ወራት የተመሠረቱ እጅግ መልካም የዓየር ንብረት የታደለች ምድር፥ የተለያዩ አዝርዕት፥ አትክልትና ፍራፍሬዎች፥ ሰብል ማብቀል የማይሳናት ኢትዮጵያ፥ የተለያዩ የቤት እንስሳትና የዱር አራዊት የሚረቡባት ሀገርና፥ ከሁሉም በላይ ደግሞ፥ ከመስከረም 1 እስከ ጳጉሜን 5–6 ድረስ ዕረፍት ሳያገኝ የሚማስን ጠንካራ ሠራተኛ ገበሬ ያለት ሀገራችን፥ የልማት ዕድገቱ ቀርቶ

ሕዝቧን እንኳን መመገብ ያልቻለችበት ምን እንደሆነ ምክንያቱን ፈልጎ መረዳት የሚያስቸግር አይደለም። የአባይን ልጅ ውሀ ጠማው እንዲሉ ዛሬ በዋና ከተማይቱ በአዲስ አበባ ሳይቀር መጠጥ ውሀ ችግር መኖሩ በወያኔም የማይካድ ነው። ለሕዝብ የቆመ፥ በሕዝብ የተመሠረተና የሕዝብ የሆነ መንግሥት ባለመኖሩ ብቻ ነው ይህ ሁሉ ችግርና በደል። ጨቋኝ አገዛዝ ተወግዶ ዴሞክራሲያው ሥርዓት ዕውን እስኪሆን ድረስ ከረሀብ፥ ከበሽታና ከድኅነት ለመውጣት የምንችል ዜጎች አይደለንም። "ዐባይ ይገደባል ሕዝቡም ይመገባል" የሚለው መፈክር ከምኞት አያልፍም።

የዋቢ ሸበሌ ጉዳይ እንደዚሁ፥ የዐባይንም ያህል እንኳን ባይሆን፥ ኢትዮጵያን እየጎዳ ባዕዳንን እየጠቀመ ለመሆኑ፥ በዓይናችን የምናየውና የምንሰማው ሀቅ ነው። ከኢትዮጵያ የማህሉና የደጋው ክፍል ተነስቶ የሀገራችንን የማያልቅ ወርቅ አፈር በገፍ እየጫነ የኦጋዴንን በረሃ አቋርጦ የኢትዮጵያን ዳር-ድንበር ተሻግሮ በመሄድ በሶማሊያ ውስጥ በለድ ወይን የሚባለውን አውራጃ በዕርሻ ሰብል በማጥለቅለቅ፥ ሶማሊያን የተለያዩ ሰብሎችና ፍራፍሬዎች ለዓለም ገበያ እንድታቀርብ አስችሏታል። ከዋቢ ሸበሌ መስኖ የሚመመረተው የሶማሌያ ሙዝ በጥራቱ በዓለም ገበያ የሚወዳደር ነው። እኛ ግን " በገዛ ዳቦየ ልብ ልቡን አጣሁት" እያልን ከመተረት ያለፈ ሥራ ሰርተን በወንዞቻችንን ለመጠቀም አልቻልንም። የኢትዮጵያን ውበትና ሃብት ጠላቶቿ የሚጠቀሙበት ሁኔታ ለመለወጥ የሚችሉት ኢትዮጵያውያን ለመሆናቸው ክርክር አያሻውም።

በእንቆቅልሽ ደረጃ ያለውን ሁኔታ ስንከታተል፥ ከላይ የተጠቀሱት የኢትዮጵያን ሀብት በማያቋርጥ መንገድ የሚጠቀሙ ሦስት ሀገሮች፥ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ዘለዓለማዊና ቋሚ ሥራ የሚሰሩ መሆናቸው ነው። ሦስቱም፥ ጠላትነታቸውን ለእነርሱ ውጤት በሚያስመዘግብ ረገድ በሚያመረቃ መልኩ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል። ብሔራዊ ጥቅማቸው ነውናም ወደፊትም በዚሁ ይቀጥላሉ። በተለየማ ወያኔ በሥልጣን እያለ ይህ የሚታሰብ አይደለም። ሦስቱም የሀገሪቱን የውስጥ ጠላቶችና ተገንጣይ ክፍሎች፥ በሚገባ አስጠግተው፥ አሰልጥነው፥ አስታጥቀውና ሌሎቹንም የገንዘብ፥ የዲፕሎማቲክና የቆሳቁስ ትብብር አድርገው ኢትዮጵያ እንድትበታተን ይህ ነው የማይባል እገዛ አድርገውላቸዋል። ምንም እንኳን ባብዛኛው የእኛው የራሳችን ጥፋት መሆኑን ልንክደው ባንችልም፥ ይህንን የጥፋትና የጥቃት ሂደት ለማስቆም ምን ይበጀናል? የሚለውን የህልውና ጥያቄ ለመመለስ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነትና ግዴታ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ታዲያ የሀገራችን ውበትና ህልውና ጠላቶቻችን እንዲያጠፉን ምክንያት የሚሆን ከሆነ፥ ምን ይሻላል? ምንስ ማድረግ ይኖርብናል? እና የመሳሰሉትን ተዛማች ጥያቂዎች ከመመለሳችን በፊት፥ በግንባር ቀደም ለጠላቶቻችን አባሪና ተባባሪ የሆነውን ወያኔን ከምኒሊክ ቤተ መንግሥት ማስወገድ የማነኛውም ዜጋ የቅድሚያ አጀንዳው መሆን እንዳለበት ማሳሰብ እንፈልጋለን። ለዚህ ተግባር የመጀመሪያው እርምጃ፥ የተበታተነው፥

የተከፋፈለውና የተዳከመው የተቃዋሚ ድርጅት በአንድ ሀገራዊ አጀንዳ ወይም ዕቅድ ዙሪያ መሰባሰብ ይዋል ይደር ሊባል አይችልም። ይህ ዕውን እንዲሆን ኢሕአፓ የተቻለውን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም። በኢሕአፓ ዕምነት፥ የሀገራችን ውበት፥ ሀብት ልምላሜና የተፈጥሮ ፀጋዎች ለሀገራችንና ለጠላቶቿ ሰለባ ሊያደርጓት ፈጽሞ አይፈቀድላቸውም። እንደ ሞኝ ተቆጥረን ጠላቶቻችን “ከሞኝ በራፍ ሞፈር እንዲቆርጡ” መፍቀድ ኢትዮጲያዊነት አይደለም። ሁላችንም ሀገራችንን ከጥቃት፥ ከውርደትና ከጥፋት ለማዳን ቆርጠን እንነሳ!!!